# በኢትዮድያ ዲሞክራሲ ለመመስረት የሚደረጉ የትግል ስልቶች ተደጋጋፊነት እና አሰፈላጊነት

ይህ ጽሁፍ በኢትዮጵያ እየተደረገ ያለዉን ዲሞክራሲን ለመመስረት በመደረግ ላይ ያሉትን የትግል ስልቶች መርምሮ ፤ የሁለቱን የትግል ስልቶች ተደጋጋፊነት እና ተቀናባሪነትን አቅርቦ ለዉጥ ለማምጣት አብሮ መስራት አስፈላጊነቱን ያቀርባል።

በኢትዮጵያ ያለውን ዘርኛ መንግስት ለማስወገድ የሚደረገው ትግል የተለያዩ ድርጅቶች የተለያዩ የትግል ስልቶች መምረጣቸዉ ይታወቃል። የሁሉም ድርጅቶች አላማ ያለዉን ዘረኛ መንግስት ማዉረድ ቢሆንም፤ የመረጡት የተለያዩ የትግል ስልቶች በድርጅቶቹ መካከል ትብብር እንዳይኅለብት ማድረጉ ግልጽ ነዉ። ዋናዉ የዚህ ጽሁፍ አላማ፤ እንዚህ የትግል ስልቶች ተደጋጋፊ መሆናቸው እና ተቀነባበረዉ የተሻለ የትግል ዉጤት ማምጣት የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል የሚል ነዉ።

<u>የትጥቅ ትግል</u>

ስልጣን በጠመንጃ አፈሙዝ፤ ይህ የትግል መንገድ ህዉሃት የተጠቀመበት እና ስልጣኑን የያዘበት መንገድ ነዉ። የስለጣን ሃይሉን ያገኘው በጠመንጃ ሃይል ነዉ ( Legitimacy through the barrel of the gun ) ይህ የትግል ስልት አሁን ግንቦት ፯ እና የአርበኞች ግንባር የሚጠቀሙበት ነዉ። ይህን የትግል ስልት እንደ አማራጭ የወሰደዉ የግንቦት ፯ ድርጅት አስረግጦ የነገረን ነገር

“ በኢትዮጵያ ውስጥ፤ አሁን ባለዉ የወያኔ መንግስት በምርጫ ህዝብ ሙብቱን ማግኘት እንደማይችል ያልፉት ሀያ አራት አመታት የታዩት ዉጤቶች የማያጠራጥሩ ግልጽ ማስረጃዎች ናቸዉ” ሲል አስቀምጦታል። ቀጥሎም የተያዘዉ የትጥቅ ትግል አገርን የማዳን መንገድ ነዉ ነው የሚለን።

ለነጻነታችን እራሳቸዉን ሊሰጡ ለተዘጋጁ ታላቅ አክብሮት ነው ያለኝ። በእዉነቱ ለነጻነቴ ህይወታቸዉን የሰጡትን ሳስብ በዉስጤ የአካል ክፍያ አብሮ ይሞታል። በአገራችን ነጻነታችን ማለት እንደሰዉ መቆጠራችን እና መታየታችን፤ ሰዉ በመሆናችን እንጂ ከየትኛዉ ዘር መምጣታችን የማይታይበት፤ እንዳሁኑ ዘረኛነት ያልነገሰበት አገር አለኝ የምንልበት ቀን ይመጣል። ባለፈዉም ኢትዮጵያ ክብራን እና ነጻነታን ጠብቃ የኖረችዉ ለነጻነት ሲሉ ህይወታቸዉን በሰዉ ክብር እና አክብሮት በሚገባቸዉ ልጆቻ ነዉ።

<u>የሰላማዊ ትግል</u>

አሁን በኢትዮጵያ ዉስጥ ይህን የትግል ስልት እንከተላለን የሚሉትን ድርጅቶች በሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል።

የመጀመሪያዉ የትግል ስልት በህዝብ ትክክለኛ ምርጫ መንግስትን ለመቀየር የሚታገሉ ድርጅቶች ናቸዉ። እነኝህ ድርጅቶች ሁሉም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ናቸዉ። ላለፉት ሃያ አራት አመታት በምርጫ መንግስት መቀየር ይቻላል ተብሎ የተደረገዉ እንቅስቃሴ የህልም እንጀራ ሆኖ መቅረቱ አሁን ለሁሉም ግልጽ የሆነ ነገር ነዉ። በተለይ ያለፈዉ ምርጫ ያሳየዉ አብይ ነገር ቢኖር ፤ በዚህ ምርጫ የተሳተፉት ድርጅቶች ምርጫው ዲሞክራሳዊ እንዲመስል አስተዋጽዎ ከማድረግ በስተቀር ምንም አይነት ዉጤት እንዳላመጡ የሚታይ ገሃድ ነዉ። ህዉሀት በምንም መንገድ በምርጫ ተሸንፎ መንግስቱን ህዝብ ለመረጠዉ ድርጅት እንደማያስረክብ በግልጽ ያሳየበት ነዉ። ለዚህም ነዉ መድረክ የራሱን ህልዉና መጠየኪያ ስብሰባ የጠራዉ። በእርግጥ እነኝህ ድርጅቶች የያዙት የትግል ስልት የትም እንደማያደርሳቸዉ አዉቀዉ የተሻለ የትግል ስልት የመቀንበር ስራ፤ ጊዜ የማይሰጠዉ አጣዳፊ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

ሁለተኛው የትግል ስልት የህዝባዊ አመጽ እና እንቢተኛነት አስተባብረን እና መርተን ዲሞክረያሳዊ መንግስትን እንመሰርታለን ብለዉ የሚታገሉ ድርጅቶች ናቸዉ። እስካሁን ድረስ ይህን የትግል ስልት በጉልህ ሲጠቀም የታየ ድርጅት የለም። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ከ ሀያ አራት አመት ይህዉሃት ዘረኛ አገዛዝ በዉሃላ ህዝብን አደራጅቶ ይዞ ሊመራ የሚችል ድርጅት በሚቻለው መንገድ በህጋዊም ይሁን በህቡ የተደራጀ ድርጅት አስፈላጊነቱ የማያጠራጥር ነው።

በዚህ በሁለተኛዉ የትግል ስልት እንታገላለን የሚሉ በዉጭ ሀገራት የሚገኙ ድርጅቶች በሰም ብቻ ያሉ ናቸው ማለት ይቻላል:: በዚህ በሚያምኑበት ሰላማዊ ትግል ህዝቡን የሚያደራጁበት ስልት አቀናብረዉ ካልሰሩ መክሰማቸዉ የማይቀር ጊዜን እየጠበቀ ያለ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነዉ። አሁን ያላቸዉ አባላት ከሚያገኛቸዉ ርካሽ የመንግስት ተቃዋሚ ነኝ ከሚል የተነሳ እርካታ በስተቀር ምንም ፋይዳ የፈጠሩት ነገር የለም።

አሁን አንድ ሳላነሳ የማላልፈዉ ጉዳይ፡ ሽንጎ የስደት መንግስት ልማቋቋም እያደረገ ያለዉን ጥረት በተመለከተ ይሆናል። እንደሚታወቀዉ የመንግስት ስልጣን የሚመነጨዉ የመጀመሪያዉ ከላይ እንደተገልጸዉ በጠመንጃ አፈሙዝ ነዉ፡ ሁለተኛው ደግሞ በትክክለኛ ምርጫ ሲሆን፤ ሶስተኛዉ ደግሞ ህዝባዊ አመጽን በሚመራ ድርጅት ይሆናል። አሁን ሽንጎ ሊያቋቁመው ያሰበዉ መንግስት ከላይ ከተጠቀሱት የመንግስት ስልጣን መያዣ መንገዶች ዉጭ ነዉ። ይህ ሽንጎ የሚቋቋመዉ መንግስት፤ መንግስት ሳይሆን የግለሰቦች ስብስብ ሆኖ ነዉ የሚቀረዉ። ገፋ ካለም የስልጣን ጥም ያለቸዉ የሰዎች ስብስብ ማጠርቀሚያ ሆኖ ጊዚያዊ መንግስት ሲምጣ በእጩነት እራሳቸዉን ለማቅረብ የተዘጋጁ የግለሰቦች ትርቅም ነዉ የሚሆንዉ ማለት ይቻላል።

አሁን ኢትዮጵያ ላለችበት የመገንጣጠል እና ህልዉናዋ ጥያቄ ዉስጥ በገባበት ጊዜ ያለዉ የትግል አማራጭ ስልት ሁለት ብቻ መሆኑ በግልጽ መታወቅ አለበት። የመጀመሪያው በትጥቅ ትግል ሲሆን ሁለተኛው በተደራጀ የህዝብ እምቢተኛነት ብቻ መሆኑ ለማንም ግልጽ መሆን አለበት።

የትጥቅ ትግሉን በመርህ ደረጃ የሚቃወሙ ድርጅቶች እና ግለሰቦች መኖራቸው ግልጽ ነው። በትጥቅ ትግል አምነዉም ከኤርትራ የሚነሳ የትጥቅ ትግል ዉጤት አይኖረዉም ብለዉ የሚቃወሙ እንዳሉ ግልጽ ነዉ። አለመደገፋቸዉን ማንም ሊረዳዉ ይችላል፡ ትግሉን መቃወማቸዉ ግን በዚህ አጣብቂኝ እና አስቸጋሪ ሁኔታ ካሉን ሁለት የትግል አማራጮች አንዱን ጨርሶ ማጥፋት እንደማለት ነዉ ። የፖለቲከኞች ዋና ስራ የሚታየዉን እና ግልጹን ማከናወን ብቻ ሳይሆን ከአስቸጋሪ ሁኔታ ተነስቶ ውጤት የማግኘት ስራ መስራት ነዉ፡ ለዚህ አሁን ግንቦት ፯ ለሚያደርገዉ ጥረት ድጋፍ ያስፈልገዋል፡ ይህን መቃወም የህዉሃትን እድሜ ማራዘም ብቻ ነው የሚሆነው። በተጨማሪ ትግላችን ጠመንጃ ይዘዉ ወያኔን ለመጣል ትንቅንቅ ከያዙት ጋር መሆን የለበትም።

አሁን በትጥቅ ትግልም ሆነ በሰላማዊ መንገድ እይታገልን ያለን ሁሉ መረዳት ያለብን ዋና ቁም ነገር እንኚህ ሁለት የትግል ስልቶች ተደጋጋፊ መሆናቸዉን ነዉ። የሁላችንም አላማ ይህን የዘረኛ መንግስት ስሩን ነቅሎ መጣል እስከሆነ ድረስ በቅንጅት እና በትብብር መሰራቱ አማራጭ የሌለዉ ጉዳይ ተደርጎ ሁሉም ይህን መንግስት እታገላለሁ የሚል ድርጅት ሁሉ በመርህ ደረጃ የሚመራበት መሆን አለበት። የዚህ ጽሁፍ ዋና አላማው የትግሎቹን ጥቅም እና ጉዳት በማግኘት ላይ ያጠነጠነ አይደለም።

የትጥቅ ትግሉን የማይቅበሉ ድርጅቶች በአዎንታ መቀበል ያለባቸዉ እዉነታ፤ ለትጥቅ ትግል ቆርጠዉ የተነሱት ድርጅቶች ዉስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ህይወታቸዉንም ሰዉተዉ ቢሆን ለኔ እና ለእናንተ ነጻነት የሞቀ ቤታቸዉን ጥለዉ የሄዱ መሆናቸዉን ለቅንጣት ያክል የሚያጠራጥር አለመሆኑ ነዉ። የሞቀ ቤታችን ውስጥ ያለነው ሰዎች፡ እነሱ ለአላማቸዉ የሚያደርጉትን ጽናትና መስዋትነትን እኛ ጥያቄ ልንጠይቃቸዉ የምንችልበት የሞራል፣ የህሊና ፣ወይም ህጋዊ መሰረቶች የሉንም።

በሰላማዊ ትግል ብለዉ የተነሱት ድርጅቶች መሰረታዊዉ ስራቸዉ ህዝቡን አደራጅቶ የተባበረ እና የተደራጀ ተቃዉሞ የማስነሳት ሥር ነው። ይህን ለማድረግ ያልተነሳ በስላማዊ መንገድ ነዉ የምታገለዉ የሚል ድርጅት ቅዠት ዉስጥ ያለ መሆኑ ግልጽ ነው። በቅርቡ ዋሽንግተን ያሉ አገር ወዳዶች፣ የዘረኝ መንግስት አግልጋይ የሆኑ ዘፋኞች ላይ ማእቀብ እንዲደረግባቸው መጠየቃቸው ይታወሳል። እንደዚህ መሰሉ ስራ በስላም እንታገላለን በሚሉ ድርጅቶች አንዱ መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው።

በእርግጥ በዉጪ አገር ያሉ ሠላማዊ መንገድ የመረጡ ድርጅቶች አገር ውስጥ ካሉ ድርጅቶች ጋር ተባብራዉ ወይም በህቡ ተደራጅተዉ ትግሉን ማጣጣፍ ዋና የትግል መስመር መሆን ያለበት ጉዳይ ነዉ። በእውነት ኢትዮጵይ ዲሞክሪያሲ ያለባት፣ እውነትኛ እኩልነት የሰፈነባት ፣ ዘረኛነት የጠፋበት አገር እንድትሆን ከፈለግን ሁላችንም ፣ ዝም ብለን የተቀመጥንውም ፣ በሰላም እንታገላለን የምንለዉም ፣ አብረን ጠመንጃ ይዘዉ ጫካ ከገቡት ጋር ትግላችንን አቀናኝተን መቀጠል ያለብን አጣዳፊ ጉዳይ ነዉ።

በሚቀጥለዉ እስከምንገናኝ ድረስ ሠላም ይግጠመን

ደ. ደመቀ

Demeked@gmail.com